G-SC[H19-67 C]

# የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ሞዴል ፈተና

የጥያቄው ብዛት፡- 40 የተፈቀደው ሰዓት፡- 1፡00

**መመሪያ አንድ፡- ከተራ ቁጥር 1-8 ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጡ።**

## የሙዚቃ ጠቢቡ

ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ በ1931 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። እናቱ ወ/ሮ ፋንታዬ ከቤተሰቡ ሁሉ የተለዩ የኪነጥበብ ሰው ነበሩ። ሀይማኖታዊ ይዘት የነበራቸው ግጥሞችና ስድ ንባቦች እንዲሁም ያሬዳዊ ዜማዎች ይፅፉ ነበር። በዚህም ለልጃቸው የዳዊትን መዝሙር በበገና ማታ ማታ ይጫወቱለት ነበር። የፕሮፌሰር አሸናፊ እናት የሞቱት እሱ የ9 ዓመት ልጅ እያለ ስለነበር የእናቱን ሞት ለመርሰት ተቸግሮ ነበር። በዚህም ምክንያት የሁልጊዜ የሙዚቃ ቅንብሮቹ ሀዘንን የሚጭሩ ናቸው። በምሳሌነት "እረኛው ባለዋሽንቱ" ሊጠቀስ ይችላል። ለኪነጥበብ መነሻውም እናቱ መሆናቸውን በተደጋጋሚ በራሱ አንደበት ይገልፅ ነበር።

ፕሮፌሰር አሸናፊ ለሙዚቃ የተለየ ፍቅር ማሳየት የጀመረው ገና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበረበት ጊዜ ነው። የተወሰኑ የሙዚቃ ትምህርቶችን በተማረበት በሐረር የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ሙዚቃ የማቀናበር ችሎታው በይበልጥ እያደገና እየጨመረ ሄደ። ከተመረቀም በኋላ በቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በአሁኑ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለሁለት ዓመት አስተማረ። ከዚያም ወደ አሜሪካ በመሄድ ኒዮርክ በሚገኘው ክሮችስተር ዩንቨርስቲ "ዘኢስት ማን ኦፍ ሚዩዚክዝ" የመጀመሪያ ዲግሪውን አገኘ። ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ የያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ተከፍቶ ስለነበር የሙዚቃ ትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ሆነ። በዚያን ጊዜም የ24 ዓመት ወጣት ነበር። ወደ አሜሪካ ከመሄዱ በፊትና ከመጣም በኋላ በርካታ መዝሙሮችን ደርሷል።

ፕሮፌሰር አሸናፊ በወጣትነት ዕድሜው የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለዓለም አስተዋውቋል። በዚህ ስራውም በንጉሡ ዘንድ አድናቆትን በማትረፉ "እረኛው ባለዋሽንት" የተባለው የመጀመሪያ ሙዚቃ እንዲያሳትም ከንጉሡ የገንዘብ ድጋር ተደረገለት። በመቀጠልም በ1962 ዓ.ም ብሔራዊ ሙዚቃ አቀናባሪ በሚል የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያ ተሸላሚ ወጣት ለመሆን በቅቷል።

/ሰለሞን ጥላሁንና ሥምረት ገ/ማርያም 2000ዓ.ም ከገፅ 272-280/

LIVEWORKSHEETS

1. የፕሮፌሰር አሸናፊ እናት ይፅፉ የነበሩት ምን ዓይነት ፅሑፎችን ነበር?

ሀ. ሃይማኖታዊ ግጥሞችና ስድንባቦችን　　ሐ. አለማዊ ዘፈኖችን

ለ. ያሬዳዊ ዜማዎችን　　መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

2. ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ የተወለዱት መቼ ነው?

ሀ. በ1913　　ለ. በ1963　　ሐ. በ1931　　መ. በ1921

3. የፕሮፌሰር አሸናፊ እናት ለልጃቸው ማታ ማታ የሚጫወቱለት ________ ነው።

ሀ. ያሬዳዊ ዜማዎችን　　ሐ. ባለዋሸንቱ እረኛ

ለ. የዳዊት መዝሙርን　　መ. ሁሉም

4. ፕሮፌሰር አሸናፊ የሁልጊዜ የሙዚቃ ቅንብሮቹን ምን አይነት ናቸው?

ሀ. ሰዎችን የሚያዝናኑ　　ሐ. ሀዘንን የሚጭሩ

ሐ. ወኔን የሚቀሰቅሱ　　መ. ሰዎችን የሚያስጨፍሩ

5. ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ከንጉሡ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት ለምንድን ነው?

ሀ. ወጣት ሙዚቀኛ ስለሆነ

ለ. በወጣትነት ዕድሜው የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለዓለም ስላስተዋወቀ

ሐ. እረኛው ባለዋሸንቱ የተባለውን የመጀመሪያ ሙዚቃ እንዲያሳትም

መ. በርካታ መዝሙሮችን ስለደረሰ

6. ፕሮፌሰር አሸናፊ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የመጀመሪያ ተሸላሚ ወጣት ለመሆን የበቃው በምንድነው?

ሀ. ለሙዚቃ የተለየ ፍቅር ስላለው　　ሐ. እናቱ በልጅነቱ ስለሞቱበት

ለ. አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ስላስተማረ　　መ. ብሔራዊ ሙዚቃ አቀናባሪ በሚል

7. የቀድሞ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩንቨርስቲ አሁን ማን ተብሎ ይጠራል?

ሀ. ሐረር የመምህራን ኮሌጅ　　ሐ. አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ

ለ. ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ　　መ. ክሮችስተር ዩንቨርስቲ

8. በምንባቡ የመጨረሻው አንቀፅ የገንዘብ ድጋፍ ተደረገለት ሲል .............

ሀ. መከታ　　ለ. አለኝታ　　ሐ. እገዛ　　መ. ሁሉም

***መመሪያ ሁለት፡-*** <u>ከ9-14 ለቀረበላችሁ ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ምረጡ።</u>


| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9. ተግዳሮት | ሀ. ደከመ | ለ. ችግር | ሐ. አረጀ | መ. ፈራ |
| 10. ጎመጀ | ሀ. ቋመጠ | ለ. መታ | ሐ. ጓጓ | መ. ሀ እና ሐ |
| 11. ደራ | ሀ. ሰፋ | ለ. ሞቀ | ሐ. ኮራ | መ. ተከሰ |
| 12. ፅሞና | ሀ. ትህትና | ለ. ምር | ሐ. ቀልድ | መ. ተመሰጠ |
| 13. ዘለፋ | ሀ. ጉዳት | ለ. ነቀፋ | ሐ. ጥላቻ | መ. ሙገሳ |
| 14. አያሌ | ሀ. ትልቅ | ለ. ጥቂት | ሐ. ብዙ | መ. ከባድ |

LIVEWORKSHEETS

**መመሪያ ሦስት፡-** <u>**ከ15-20 ለቀረቡላችሁ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ምረጡ፡፡**</u>

15. ህቡዕ ሀ. ገሀድ ለ. ስውር ሐ. ድብቅ መ. የማይታይ
16. ቆንቋና ሀ. ንፉግ ለ. ስስታም ሐ. ለጋስ መ. ገብጋባ
17. አመሰገነ ሀ. አወደሰ ለ. አሞገሰ ሐ. አማረረ መ. አለቀሰ
18. ሁከት ሀ. ቂም ለ. ረብሻ ሐ. አምበጓሮ መ. ሰላም
19. መቀላቀል ሀ. ማዋሀድ ለ. መጨመር ሐ. መለያየት መ. መበከል
20. ከባድ ሀ. ቀላል ለ. ትንሽ ሐ. ጥቂት መ. ብዙ

**መመሪያ አራት፡-** <u>**ከተራ ቁጥር 21-40 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ጥያቄ በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡**</u>

21. አንድ አይነት የሆኑ ነገሮች በጋራ የሚጠሩበት መጠሪያ ስም .............. ይባላል፡፡
    ሀ. የተፀውኦ ስም ሐ. የጥቅል ስም
    ለ. የወል ስም መ. የነገር ስም
22. ቢጋር በምን መልኩ ልናዋቅር እንችላለን?
    ሀ. በርዕስ መልክ ሐ. በዐረፍተ ነገር መልክ
    ለ. በድርሰት መልክ መ. ሀ እና ሐ
23. ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ለተፀውኦ ስም ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ........... ነው፡፡
    ሀ. ተማሪ ለ. ገበሬ ሐ. ነጋዴ መ. አባይ
24. ከዚህ በታች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ነፃ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው?
    ሀ. ተራራ ለ. መንገደኛ ሐ. መምህራን መ. ልብሳቸው
25. ወታደሮቻችን የሚለው ቃል በምዕላድ ተነጣጥሎ ሲፃፍ ትክክለኛው የቱ ነው?
    ሀ. ወታደሮች-አችን ሐ. ወታደር-ኦቻችን
    ለ. ወታደር-ኦች-ኣች-ን መ. ወታደር- ኦች-ኣችን
26. ሀይለ-ቃሉ መጀመሪያ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ የትኛውን ይመስላል?
    ሀ.  ለ.  ሐ.  መ. 
27. በመነገር፣ በመተረት ወይም በመዜም የሚከናወን ቃላዊ ፈጠራ ምን ይባላል?
    ሀ. ሙዚቃ ለ. ሥነ-ቃል ሐ. ሥነ-ግጥም መ. ሥነ-ፅሑፍ
28. ይችን ማጭዴን ሆዷን አሚታል፣
    እየቆረጠ ያጋድማታል፡፡
    ይህ ቃላዊ ግጥም የ ________ ነው፡፡
    ሀ. የፉከራ ቃላዊ ግጥም ሐ. የአጨዳ ግጥም
    ለ. የሙሾ ግጥም መ. የዘፈን ግጥም


LIVEWORKSHEETS

29. አይኔን ግንባር ያርገው ብላችሁ አትማሉ፣

ይቸግራል እና ________፡፡

ይህን ቃላዊ ግጥም በክፍት ቦታው ገብቶ ሊያሟላ የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. ለምንድን አትበሉ ሐ. ወዴት ነው አትበሉ

ለ. ከእኔ አትጣሉ መ. መሪ ማባበሉ

30. በበጋ እራስ ቢሉት ፀሐይ እየፈራ፣

በሐምሌ እራስ ቢሉት ዝናብ እየፈራ

ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ

ይህ ቃላዊ ግጥም ለምን ዓይነት ሰው የሚገጠም ይመስላችኋል?

ሀ. ለብልጥ ገበሬ ለ. ለሰነፍ ገበሬ ሐ. ለሞኝ ገበሬ መ. ለታታሪ ገበሬ

31. የአለምህ አባት ሲሰራ ንብ ነው፡፡ በዚህ ዐ.ነገር ንብ የሚለው ቃል አውዳዊ ፍች ምንድነው?

ሀ. በራሪ ነፍሳት ለ. ጎበዝ ሐ. ታታሪ መ. ለ እና ሐ

32. የአንድን ነገር ምንነት፣ የአሰራር ሒደት የሚገልፅ ሁነቶችን፣ ድርጊቶችን በተመለከተ መልስ የሚሰጥ የድርሰት ዓይነት ________ ነው፡፡

ሀ. አመዛዛኝ ድርሰት ሐ. ገላጭ ድርሰት

ለ. ተራኪ ድርሰት መ. ስዕላዊ ድርሰት

33. አንድን ሁነት በጊዜና በቦታ ቅደም ተከተል እንዲህ ሆነ እንዲህ ተደረገ በሚል የሚያቀርብልን የድርሰት አይነት .......... ነው፡፡

ሀ. አመዛዛኝ ድርሰት ሐ. ሥዕላዊ ድርሰት

ለ. ተራኪ ድርሰት መ. ገላጭ ድርሰት

34. በፅሑፍ ውስጥ ሀሳቡ እንዳያሻማና መልዕክቶች እንዳይዛቡ ለአንበቢ ግልፅ እንዲሆን ጉልህ ድርሻ ያለው ________ ይባላል፡፡

ሀ. ሥርዓተ ነጥብ ለ. ሥነ-ሥርዓት ሐ. አንቀፅ መ. ዐ.ነገር

35. ተውሳከ ግሶች ከግስ በፊት እየገቡ ግሱን ከምን አንፃር ይገልፁታል?

ሀ. ከጊዜ ለ. ከቦታ ሐ. ከሁኔታ መ. ሁሉም

36. አንድ ነገር መቼ እንደተከሰተ ወይም እንደሚከሰት የሚገልፅ ________ ይባላል፡፡

ሀ. መስተዋድድ ለ. ቅፅል ሐ. የጊዜ ተውሳከ ግስ መ. ስም

37. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማመዛዘን የትኛው እንደሚሻል የሚያሳይ የድርሰት ዓይነት ________ ይባላል፡፡

ሀ. ገላጭ ድርሰት ሐ. አመዛዛን ድርሰት

ለ. ተራኪ ድርሰት መ. ሥዕላዊ ድርሰት

LIVEWORKSHEETS

38. ብሩክ የተመሰገነ በስነ-ምግባሩ ነው፡፡ ይህ የሰዋሰው ስህተት ያለበት ዐ.ነገር ተስተካክሎ ሲፃፍ ________ ነው፡፡

ሀ. ብሩክ በሥነምግባሩ ነው የተመሰገነ፡፡

ለ. ብሩክ በስነምግባሩ የተመሰገነ ነው፡፡

ሐ. ነው ብሩክ የተመሰገነ፡፡

መ. ብሩክ የተመሰገነ ነው በሥነምግባሩ

39. ኢ/ስ/መ/ጉ ይህ በአህፅሮት ቃል የተፃፈ ፅሁፍ ተብራርቶ ሲፃፍ ከሚከተሉት ትክክል ሆነው የቱ ነው?

ሀ. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ

ለ. የኢትዮጵያ ሰውነት መጠበቂያ ጉዞ

ሐ. የኢትዮጵያ ሰዎች መመለሻ ጉዳይ

መ. የኢትዮጵያ ሰዎች መኖሪያ ፈቃድ ጉዳይ

40. እኔ መፅሐፍ እያነበብኩ ነው፡፡ ይህ ዐረፍተ ነገር የተፃፈው በ ________ ጊዜ ነው፡፡

ሀ. በኃላፊ ጊዜ

ለ. በትንቢት ጊዜ

ሐ. በአሁን ጊዜ

መ. መልሱ አልተሰተም

LIVEWORKSHEETS